# *አማርኛ*

## በምዕራብ አውስትራሊያ ውስጥ የመንግስት ሥራ ዕድሎች

**Jobs.wa.gov.au** በምዕራብ አውስትራሊያ ውስጥ ስለመንግስት ሥራ ዕድሎች መረጃ የሚገኝት መንገድ ነው:: በክፍለ ሀገሩ ትልቁ ሥራ ቀጣሪ መሥሪያ ቤት ነው::

በማስታወቂያው ላይ ካልተገለጸ በስተቀር **Jobs.wa.gov.au** ላይ የሚወጡ የሥራ ማሰታወቂያዎች ላይ ማንኛውም ሰው ሊያመለክት ይችላል:: የቅጥር መስፈርት ሙያ: ዕውቀት: እና ችሎታ: እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ልዩ መመዘኛዎች ላይ የተመሰረተ ነው::

በምዕራብ አውስትራሊያ መንግስት ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት እንዲችል የየብሔሩ ተወካዮች የሚገኙበት የሠራተኛ ኃይል ይፈልጋል:: ስለዚህ የተለያ ባህል ያላቸው ሰዎች: ያገሪትዋ ተወላጆች እና አከለ ስንኩላን ለስራ እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ::

አውስትራሊያ ዜግነት ወይም ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ቋሚ ሥራ ለመያዝ ዋና አስፈላጊ መመዘኛ ነው::

የአውስትራሊያ ነዋሪነት የሌላቸው ግን ተገቢው ቪዛ ያላቸው ሰዎች ለተወሰነ ጊዜ ቅጥር ብቻ ነው ብቁ የሚሆኑት::

### የምዕራብ አውስትራሊያ መንግስት የሥራ ድሕረ ገጽ

በምዕራብ አውስትራሊያ መንግስት የሥራ ድህረ ገጽ ውስጥ በተለያየ መንገድ ሥራ መፈለግ ትችላላችሁ::

### በሥራ ድሕረ ገጽ ላይ የሥራ ፍለጋ ዘዴዎች

**ሁሉንም ክፍት ስራዎች ለማየት:**

ምንም ስራ ከመምረጣችሁ በፊት በኮምፒተሩ ማመልከቻ ማውስ (MOUSE) “Search” የሚለውን ምረጡ::

**በምርጫ ላይ የተመስረተ ክፍት ስራዎችን ለማየት:**

ያሉትን ክፍት ሥራዎች በሙያ: በደመወዝ መጠን: በሥራ ቦታ: በድርጅት: በሥራ አይነት ወይም በምደባ ደረጃ በመለያት መፈለግ ትችላላችሁ::

**ማስታወሻ:** በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ ብዙ ምርጫዎችን ለመምረጥ በኮምፒተሩ ታይፕ ማድረጊ (keyboard) ላይ የሚገኘውን “CTRL” የሚለውን ተጭኖ በመያዝ በማውስ አማከይነት የምትፈልጉትን ስራ መምረጥ ትችላላችሁ::

## በቅርብ የወጡትን ሥራዎች ለማየት

በማውስ “View Latest Jobs” የሚለውን በግራ እጅ በኩል በቀጥታ ከለው ዝርዝር ውስጥ መምረጥ::

## ክፍት ሥራዎች በኢሜል እንዲላኩላችሁ ስለመመዝገብ

የእናንተን መስፈርት የሚያሟሉ የሥራ ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ጊዜ በኢሜል መልእክት እንዲደርሳችሁ ማድረግ ትችላላችሁ:: ይህንን ለማድረግ በግራ እጅ በኩል በቀጥታ ከለው ዝርዝር ውስጥ “Email me Jobs” የሚለውን በማውስ አማከይነት በመምረጥ: የእናንተን ዝርዝር ሁኔታ በመሙላትና ትዕዛዛቶቹን በመከተል መመዝገብ ትችላላችሁ:: ከዚያ የግል መለያ ኮድ (password) በኢሜል ይላክላችኋል:: ይህንን ኮድ በመጠቀም ኮምፒተሩ ላይ መስመር ማግኘት ትችላላችሁ ከዚያ የራሳችሁን መስፈርት የሚያሟሉ የሥራ መፈለጊያ መስፈርት መፈጠር ትችላላችሁ::

## የራሳችሁን መስፈርት የሚያሞላ የሥራ መፈለጊ ስለመፈጠር

“Login” የሚለውን በመምረጥ ከዘያ “My Details” የሚለውን ምረጡ ከዚያ “My Search Profile” የሚለውን ምረጡ:: “Ctrl” የሚለውን በመጫን በርከት ያለ የሥራ ዘርፍ ለመምረጥ ወይም በማስታወቂያ ላይ ያሉት ስራዎች ሁሉ እንዲደርሱዋችሁ “Select all Fields” የሚለውን ምረጡ: ከዚያ “Email me Jobs” ለሚለው “Yes” ወይም “ No” ምረጡ ከዚያ “Save Profile” የሚለውን ምረጡ::

የሥራ መፈለጊያውን መስፈርት በፈለጋችሁ ጊዜ በምዕራብ አውስትራሊያ መንግስት የሥራ ድህረ ገጽ ላይ ወደ ኋላ በመመለስ በቀላሉ መለወጥ ትችላላችሁ::